# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 304 የካቲት 28 2006 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና ሞክራሲ ንቅናቄ ከሰሞኑ በደረሰው መረጃ ወያኔ ከአማራው ቀምቶ በትግራይ ክልል ባስገባቸው ወረዳዎች ላይ የሚኖሩ ንጽሃን ዜጎች ለምን በወያኔ የግፍ አገዛዝ ትማረራላችሁ እየተባሉ በወያኔ ታማኝ ሚሊሻዎች እስር እንግልትና ድብደባ እየተፈጸመባቸው መሆኑን አረጋግጦአል። በዚህ በአዲስ መልክ በተጀመረዉ የወያኔ የጥቃት ዘመቻ መሳሪያ ያነገቡ የህወሃ ሚሊሻዎች ከክልላቸዉ ዉጭ ወደ ተለያዩ የአማራ ከተማዎችና ወረዳዎች ሰርገዉ እየገቡ የእነሱን ቋንቋ የማይናገረዉን ሁሉ የግንቦት 7 ተላላኪዎች ናችሁ በሚል እያሰሩ በመደብደብ ላይ ናቸዉ።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ቁጫ ወረዳ ዉስጥ አንድ ወጣት እራሱን፤ ወላጅ እናቱንና ከብቶቹን በእሳት አጋየ

በደቡብ ክልልዋ ቁጫ ወረዳ የማንነት ፣ የመልካም አስተዳደርና የልማት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የተነሳውን የህዝብ ብሶትና ተቃውሞ አሁንም ድረስ ማብረድ ያልተቻለ ሲሆን፣ ፋሽስቱ ወያኔም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጸረ ሰላም ሃይሎች እጅ አለበት በሚል ስጋት በአካባቢው ነፍሰ ገዳይ ቅጥረኛ የጸጥታ ሃይሎች በማሰማራት ሰላማዊው የወረዳዋን ህዝብ እያሸበረ፡ እያስደበደበና እያስገደለ እንደሚገኝ በተደጋጋሚ በአካባቢው የሚገኙ ዘጋቢዎቻችንን ዋቢ በማድረግ መዘገባችን ይታወሳል።

ከሰሞኑ የወረዳዋ ነዋሪ የሆነው ወጣት እዮብ ብርሃኑ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን የባህል ዘፈን በሚዘፍኑበት ወቅት ለምን ትዘፍናላችሁ በሚል በቅጥረኛ የጉጅሌው ወያኔ ፖሊስ በከፋ ሁኔታ መደብደቡን ተከትሎ ወሰደው በተባለው እርምጃ በየካቲት 21 ቀን 2006 ዓ. ም ምሽት ላይ ፡ ራሱን ጨምሮ እናቱን፣ 8 የቀንድ ከብቶችንና ሌሎች ንብረቶችን በእሳት አጋይቷል። የሟቾቹ ቀብር የካቲት 22 ቀን በቦላን ቀበሌ የተፈፀመ ሲሆን ከግጭቱ ጋር በተያያዘ የአንድ ሰው ህይወት ያጠፋው ፋሽስቱ ወያኔ ወታደርም እስካሁን ለፍርድ አለመቅረቡን ለማወቅ ተችሏል።

በቁጫ ወረዳ የሚገኙ ወጣቶች የአካባቢያቸውን ባህላዊ ዘፈን በጋራ እየዘፈኑ ሲሄዱ በአረመኔ የጉጅሌው ወያኔ ፖሊሶች ታፍሰው እንደተደበደቡና ለእስር እየተዳረጉ መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል። በወረዳው እየተካሄደ ባለው መጠነ ሰፊ አፈሳና ከፍተኛ ድብደባን ተከትሎ ወጣቶች በቂ ህክምና ስለማያገኙ በርካቶቹ በለጋ እድሜያቸው የአገዛዙ ሰለባ እየሆኑ ነው ሲል ዘጋቢያችን አድርሶናል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## አዲስ አበባ ዉስጥ አንድ የወያኔ ታጣቂ ባልና ሚስትን በአሰቃቂ ሁኔታ በጥይት ደብድቦ ገደለ

በአዲሳባ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ልዩ ስሙ መካኒሳ አቦ ማዞሪያ በሚባል አከባቢ ነዋሪ እንደሆኑ የተነገረውና፡ ሶስት ልጆችን አፍርተው በሰላም ኑሩዋቸውን የሚመሩ ባልና ሚስት በፋሽስቱ ወያኔ ቅጥረኛ ታጣቂ በጥይት ተደብድበው መገደላቸው ታወቀ። ለቀብር የወጣው ሕዝብ በፋሽስቱ ወያኔ ቅጥረኛ አረመኔ የፌደራል ፖሊሶች የተበተኑ ሲሆን አስከረኖቹ አለመቀበራቸውም ታውቋል።

ተጠርጣሪ ገዳይ ከሟቾች አጥር ጋር የተያያዘ የቀበሌ ቤት ተከራይቶ ሲኖር፣ መውጫና መግቢያው በሟቾች ግቢ ውስጥ እንዲሆን ለክፍለ ከተማው ወረዳ ሦስት በማመልከቱ ይፈቀድለታል፡፡ሆኖም ሟቾቹ ባልና ሚስት የወረዳውን ውሳኔ በመቃወምና ድርጊቱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ፣ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት በመውሰድ ተጠርጣሪውንና ወረዳውን ይከሳሉ፡፡ ፍርድ እንደ ሰማይ በራቀባት ኢትዮጵያ ዉስት የክስ ሒደቱ ላለፉት በርካታ ወራት የተጓተተ ቢሆንም፣ ፍርድ ቤቱ ሁለቱም ወገኖች ማለትም ተጠርጣሪ ገዳይና ሟቾች ምንም ዓይነት ግንባታ ወይም የማፍረስ ድርጊት እንዳይፈጽሙ ዕግድ ጥሎበት እንደነበርም ከአካባቢው ነዋሪዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ተጠርጣሪ ገዳይ ከወትሮ ለየት ባለ ሁኔታ የካቲት 24 ቀን 2006 ዓ.ም. ዕግድ የተጣለበትን የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በመተላለፍ፣ አጥር ለማጠባበቅ ሲሞክሩ ሟች አቶ ዳንኤል ‹‹ዕግድ የተጣለበት ስለሆነ በሕግ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ አጥር ማጠርም ሆነ ማፍረስ ተከልክሏል፡፡ በሕግ አምላክ አትንካ፤›› በማለት ሲናገሩ መስማታቸውን የአካባቢው ነዋሪዎች ገልጸዋል።

ተጠርጣሪው ቤቱ በመግባት ክላሽኒኮቭ ጠመንጃውን ይዞ በመውጣት አቶ ዳንኤልን ከአራት በላይ በሆኑ ጥይቶች ከገደለ በኋላ፣ የተኩስ ድምፅ ሰምተው ወደ ቤት በመግባት ተደብቀው የነበሩትን ወ/ሮ ምስለን በተመሳሳይ ደብድቦ መግደሉን ነዋሪዎቹ ገልጸዋል፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## 118ኛው የአድዋ ድል በዓል ባለፈው እሁድ በደማቅ ሁኔታ ተከብሮ ዋለ

ጥቁር ሕዝብ ነጭን ሊያሸንፍ ይችላል የሚለውን እሳቤ ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም ህዝቦች ሕሊና ማስቀመጥ የተቻለበትና ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያዊያን አንገታችንን ቀና አድርገን በኩራት እንድንራመድ ያስቻሉን ጀግኖች አባቶቻችን ወራሪው ፋሽስት ኢጣሊያን አድዋ ላይ አይቀጡ ቅጣት ቀጥተው አሳፍረው ያባረሩበት 118ኛው የአድዋ ድል በዓል በኢትዮጵያና በሌሎችም በዓለም ዙሪያ በሚገኙ ሀገሮች በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ባለፈው እሁድ የካቲት 23፣ 2006 ዓ/ም በድምቀት ተከብሮ መዋሉን ከያቅጣጫው ካገኘናቸው መረጃዎች ማወቅ ተችሏል።

ማንም በፋሽስታዊ አገዛዝ ስር ያለ ሁሉ መብቱን ለማስከበር ቁርጠኛ መሆን እንዳለበትና አስፈላጊውን መስዋትነትም መክፈል እንደሚገባው በማስተማሩ በኩል ወደር የማይገኝለት ይህ የአድዋ ድል መታሰቢያ እለት በዓለም ጥቁር ሕዝቦች ሳይቀር ታላቅ አክብሮት እንደሚሰጠው ከተሌያዩ ምንጮች ለማወቅ ተችሏል።

በነጻነት እጦት ሲሰቃዩ ለነበሩት የአፍሪካ ሕዝቦችና በሌሎችም አህጉሮች ለሚኖሩ ጥቁሮች የነጻነትን ቀንዲል ለኩሶ ይቻላልን በተግባር መስበክ የቻለው ይህ ክስተት ሁሌም በኩራት የሚንጠን ያባቶቻችን ያይበገሬነት ውጤት ቢሆንም ይህ ያባቶቻችን የጀግንነት ትሩፋት እንጅ የኛ እንዳልሆነም ልናስተውል ይገባል የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም። ይህን አስተያየት የሚጋሩ ሌሎች ደግሞ ዛሬ በሀገራችን ከፋሽስት ጣሊያን ያላነሰ ግፍና በደል እያደረሰ ያለው ፋስስት ወያኔ ሕዝባችንን በርሃብ እየጠበሰ፣ በእስራትና ሞት እየቀጣ፣ በስደትና እርዛት እያሰቃየው ባለበት ባሁኑ ወቅት ይህን አገዛዝ ሳናስወግድ በትዝታ ሰምጠን በአድዋ ድል ጮቤ መርገጥ ትላንትን እየናፈቁ ዓይናችን ስር ጉድ እያሳየን ያለውን ዛሬን መርሳት ነው ስለሆነም የቅብጠት ይመስላል” ይላሉ።

( ወደ ገጽ 3 ዞሯል )

## ከበረራ ቁጥር 702 አውሮፕላን ጠለፋ ወዲህ አየር መንገድ እየታመሰ መሆኑ ተሰማ

የጠለፋውን ድራማ በመንፈስ ጭንቀት ወይም በእብደት የተነሳ የተደረገ ለማስመሰል የጠላፊውን እህትና ወንድም በምስክርነት ፊታውራሪ አድርጎ ያቀረበው የወያኔው ሚዲያና የማህበራዊ መገናኛ ድረ ገጾች ወኪሎቹ፤ ሲያስተላልፉት የነበረው መረጃ ሁሉ ወደ ኋላ ባርቆ፤ ሲገለገል በነበረው ዓለማቀፍ ተጠቃሚ ዘንድ እስከዛሬ ስንበር የነበረው ለካ በንኮች ነበር የሚል ትርጉም እየፈጠረ በመምጣቱ ወያኔ ሕወሃት ይህን መሰሉን የውሸት ስብከት ለማቆም ከመገደዱም በላይ በምን መልኩ ማስተባበያ እንደሚያቀርብ በመነጋገር ላይ እንደሆነ ውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ገለጹ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አንድ ሰው አንድን ድርጊት ከመፈጸሙ በፊት ምን ለማድረግ እንዳሰበ ለማወቅ ባለመቻሉ የተቸገረው ሕወሃት ከበረራ ቁጥር 702 የመንገደኞች አውሮፕላን ጠለፋ ጋር በተያያዘ ምን ማድረግ እንዳለበት ቢቸግረው በወያኔው አየር መንገድ ላለፉት አስር ዓመታት የካፒቴኖች ሐላፊ ሆኖ ሲያገለግል የነበረውን ካፒቴን ደስታ ዘሩን በማባረር ችግሩን ለመፍታት የሞከረ በመምሰል ድርጅቱን በማመስ ላይ መሆኑ ታውቋል። በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየታቸውን የሰጡ ግለሰቦች እንደሚሉት ግን “በአየር መንገዱ፣ ዘረኝነት ነግሷል፣ ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ጣሊያን አባይ ወንዝን አስመልክቶ ኢትዮጵያንና ግብፅን ለመገላገል ፍላጎተ እንዳላት ተናገረች

የጣሊያን መንግሰት አባይ ወንዝ ላይ በመገንባት ላይ ያለዉን ግዙፍ ግድብ ተከትሎ በኢትዮጵያና በግብፅ መካካል የተፈጠረዉንና አላስፈላጊ መልክ እየያዘ በመያዝ ላይ ያለዉን ንትርክ በሰላማዊ መለስከ ለመፍታት ፍላጎት እንዳላለት ገለጸች። ጣሊያን ይህንን ፍላጎቷን የገለጸችዉ ባለፈዉ ባለፈው ሳምንት የግብፅ ባለሥልጣን በጣሊያን ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት መሆኑ ታዉቋል። በጉብኝቱ ወቅት የጣሊያን ባለስልጣኖች መንግሥታቸዉ የተፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት ከመሞከር ውጪ የተለየ ሚና እንደማይኖረው አስታውቀዋል፡፡ የግብፅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ነቢል ፋህሚ የሚመሩት ቡድን ከሳምንት በፊት ወደ ጣሊያን መጓዛን፣ ከጣሊያን መንግሥትም መልካም ምላሽ ማግኘቱን ለሚዲያዎች መናገራቸውን ጠቅሰን መዘገባችን ይታወሳል፡፡ በግብፅ የጣሊያን አምባሳደር ሞሬትዚዮ ማሳሪ በበኩላቸው ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት መግለጫ፣ የመንግሥታቸው አቋም በኢትዮጵያና በግብፅ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ወያኔ በግንቦት 7 ስም ሠላማዊ ዜጎችን ማሰቃየቱን ባስቸኳይ ማቆም አለበት

ባለፉት አራትና አምስት አመታት በግልጽ እንዳየነዉ የኢትዮጵያ ህዝብ እኩልነቱን፤ መብቱንና ነጻነቱን ለማስከበር የሚያደርገዉ ትግል ጫና በፈጠረበት ቁጥር ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የራሱን ህገመንግስት የሚደፈጥጡ ህጎች አርቅቆ አያጸደቀ ሠላማዊ ዜጎችን አስሯል፤ ገድሏል ከአገር እንዲሰደዱም አድርጓል። ለምሳሌ በ2003 ዓም የኢትዮጵያ ፓርላማ ከቤተመንግስት የተላለፈለትን ትዕዛዝ አክብሮ ለኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ነፃነት መከበር የሚታገለዉን የግንቦት 7 ንቅናቄ ሽብርተኛ አድርጎ ፈርጇል። ይህ ፈር የለቀቀ ፍረጃ ደግሞ ወያኔ የሱን ዘረኛ ስርዐት የሚቃወሙ ግለሰቦችን፤ ሀሳባቸዉን በነፃነት የሚገልጹ ዜጎችን፤ ጋዜጠኞችን፤ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችንና ከወያኔ ጋር አናብርም ያሉ ወጣት ኢትዮጵያዉያንን "ግንቦት ሰባቶች" ናችሁ እያለ በጅምላ እያሰረ እንዲያሰቃይ ህጋዊ ሽፋን ሰጥቶታል። ለምሳሌ ከፍትህና ከነጻነት ጥማት ዉጭ ከግንቦት 7 ንቅናቄ ጋር ምንም አይነት ግኑኝነት የሌለዉን የፖለቲካ ፓርቲ መሪዉን አንዱአለም አራጌን፤ ታዋቂዉን ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋንና መምህርት ርኢዮት አለሙን የግንቦት 7 አባላት ናቸዉ የሚል ሰንካላና መሠረተ ቢስ ክስ መስርቶ ለረጂም ዘመን እስራት ዳርጓቸዋል።

ወያኔ እንደ ዛሬዉ ከተማ ዉስጥ ሆኖ ሥልጣን ሳይቆጣጠር ገና ጫካ ዉስጥ እያለ ጥርሱን ከነከሰባቸዉና ከተቻለ አጠፋቸዋለሁ ካለዚያም አሽመደምዳቸዋለሁ ብሎ አስራ ሰባት አመት ሙሉ ከተዘጋጀላቸዉ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ የአማራ ብሄረሰብ ነዉ። በለስ ቀንቶት ሥልጣን ከጨበጠ ማግስት ጀምሮም በወሎና በጎንደር በኩል ከትግራይ ጋር የሚያዋስኑ ሰፊ የሆነ ለም መሬቱን ጠቅልሎ በመውሰድ ዘረኛ ሥርዓቱን ዕድሜ ሊያራዝሙልኛል ይችላሉ ብሎ የሚተማመንባቸውን የቀድሞ የትግል አጋሮቹንና ካድሬዎቹን አስፍሮበታል:: ይህ በደልና ግፍ አልበቃ ብሎትም ቀደምቶቹ የኢትዮጵያ ገዥዎች ለፈጸሙት ግፍና የአስተዳደር በደሎች ሁሉ አማራዉን በጅምላ ተጠያቂ የሚያደርግ ፕሮፖጋንዳ እነሆ እስከዛሬ በመርጨት ለዘመናት በሠላም ከኖረው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር በጠላትነት እንዲተያይ አድርጎታል:: በወያኔ አጋፋሪነት በበደኖ ፡በአርሲ በአረካና ሌሎች አካባቢዎች አማራው ላይ በግፍ የተፈጸመው ጭፍጨፋና ከ2004 እስከ 2005 ዓም አማራዉን ከጉራፈርዳና ከቤንሻንጉል ለማፈናቀል የተወሰደው እርምጃ የዚህ የወያኔ የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ ውጤት መሆኑን የምስት የለም::

ሟቹ መለስ ዜናዊና በህይወት የሚገኙ ቀንደኛ የወያኔ መሪዎች የተጠናወታቸው የአማራ ጥላቻ በጸረ ፋሽስት ዘመቻ ወቅት ባንዳ ከነበሩ አባቶቻቸዉና አያቶቻቸዉ የተወረሰ ፋሽስት ጣሊያን ለደረሰባት ሽንፈት በዘርና በሃይማኖት ተከፋፍለን እርስ በርሳችን እንድንጠፋፋ ተክላብን የሄደቺው ተንኮል አካል ነው::

የዚህ የጥፋት አጀንዳ አስፈጻሚ የሆነው ወያኔ የጀመረውን አገር የማፍረስና ህዝብ የመከፋፈል አጀንዳ ለማሳካት በየክልሉ የተኮለኮሉ ምስሌኔዎች እንወክለዋለን በሚሉት ህዝብና ክልል ላይ እየፈጸሙት ያለው በደልና ሰቆቃ አዲስ ምዕራፍ በያዘበት በአሁኑ ወቅት እራሳቸውን ለባርነት አዋርደው ህዝባቸውን በማዋረድ ላይ የሚገኙት የብአዴኑ አለምነህ መኮንንን የመሳሰሉ ሆድ አደሮች ውርደት በቃን ዘረኝነት በቃን ብለው በተነሱ ዜጎች ላይ እየወሰዱ ያለው ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ እጅግ አሳሳቢ ሆኖአል::

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና ሞክራሲ ንቅናቄ ከሰሞኑ በደረሰው መረጃ ወያኔ ከአማራው ቀምቶ በትግራይ ክልል ባስገባቸው ወረዳዎች ላይ የሚኖሩ ንጽሃን ዜጎች ለምን በወያኔ የግፍ አገዛዝ ትማረራላችሁ እየተባሉ በወያኔ ታማኝ ሚሊሻዎች እስር እንግልትና ድብደባ እየተፈጸመባቸው መሆኑን አረጋግጦአል:: በዚህ በአዲስ መልክ በተጀመረዉ የወያኔ የጥቃት ዘመቻ መሳሪያ ያነገቡ የህወሃ ሚሊሻዎች ከክልላቸዉ ዉጭ ወደ ተለያዩ የአማራ ከተማዎችና ወረዳዎች ሰርገዉ እየገቡ የእነሱን ቋንቋ የማይናገረዉን ሁሉ የግንቦት 7 ተላላኪዎች ናችሁ በሚል እያሰሩ በመደብደብ ላይ ናቸዉ።

ይህ በመሆኑ ዛሬ አትዮጵያን ከሱዳንና ትግራይን ከጎንደር ጋር በሚያዋስኑ የአማራ ክልል ዉስጥ የሚገኙ ገበሬዎች እጃቸዉ እርፍ ከሚጨብጥበት ግዜ በወያኔ ሰንሰለት የሚታሸበት ግዜ ይበልጣል፤ የመንግስት ሰራተኛዉና የከተማ ነዋሪዉም ቢሆን አብዛኛዉን ግዜ የሚያጠፋዉ ከወያኔ ካድሬዎች ጋር ግምገማ በመቀመጥ ሲሆን ተማሪዉና ወጣቱ ህብረተሰብ ደግሞ "መጡ አልመጡም" እያለ ሌሊቱን የሚያሳልፈዉ በየጫካዉ እየተሸሸገ ነዉ።

የዚህ አይነት አስከፊ ግፍና መከራ በአፋር ፡ በጋምቤላ በኦጋዴንና በኦሮሚያ በሚኖሩ ዜጎቻችን ላይ ሲፈጸም ቆይቶአል:: ወያኔ እራሱ አርቅቆ ባጸደቀውና በሐምሌ ወር 1987 ዓም በስራ ላይ የዋለዉ የወያኔ ህገ መንግስት ኢትዮጵያ በዘጠኝ የፌዴራል ክልሎች መከፈሏንና እያንዳንዱ ክልል እራሱን በእራሱ የማስተዳደር መብቱ የተረጋገጠ እንደሆነ ይደነግጋል። በዚህ ህገ መንግስት መሠረት እያንዳንዱ ክልል የራሱ ቋንቋ፤ የአስተዳደር ማዕከልና እንዲሁም የክልሉን ሠላምና ጸጥታ የሚያስከብር የፖሊስ ኃይል ይኖረዋል ይላል። ታድያ ለምንድነዉ እያንዳንዱ ክልል የራሱ ፖሊስ ኃይል እያለዉ ከትግርኛ ቋንቋ ዉጭ ሌላ ቋንቋ የማይናገሩ የህወሃት ታማኝ ሚሊሻዎች አማራ ክልል ዉስጥ እየገቡ አማራዉን የሚያሰቃዩት?

መልሱ ቀላል ነዉ። ኢትዮጵያ ዉስጥ ህዝባዊ አምቢተኝነቱ እያየለ በመጣና የነጻነት ኃይሎች ጡንቻ በፈረጠመ ቁጥር ወያኔ አንገቷ ላይ ቀጭል እንደታሰረባት በቅሎ ይደነብራል። የደነበረ ደግሞ መራገጡ አይቀርምና መሳሪያ ያነገቡ ኃይሎችን እንቅስቃሴ እገታለሁ በሚል ከንቱ ጥረት ደንባራዉ ወያኔ የፈሪ በትሩን በድንበር አካባቢ በሚኖሩ የአማራ ክልል አርሶ አደሮች፤ ወጣቶችና ሠራተኞች ላይ ማሳረፍ ጀምሯል።

ወያኔ እንደ ግንቦት ሰባት የኮነነዉና የህዝብና የአገር ጠላት አድርጎ የሳለዉ ድርጅት የለም፤ የወያኔ የዜና ማሰራጫዎችም ይህንን የአገዛዙን አቋም በተደጋጋሚ ለኢትዮጵያ ህዝብ አሰምተዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ማን ለመብቱና ለነጻነቱ እንደቆመና ማን መብቱና ነጻነቱ ላይ እንደቆመበት ለይቶ የሚያዉቅ ህዝብ ነዉ። ስለዚህም ግንቦት ሰባት ወያኔዎች አላፊዉንና አግዳሚዉን "ግንቦት ሰባት" ነህ እያሉ ከሚያሰቃዩ፤ ህዝብንና ግንቦት ሰባትን ያስተሳሰረዉ ነጻነት፤ ፍትህና ዲሞክራሲ ነዉና የኢትዮጵያን ህዝብ ጥያቄ ቢመልሱ ለእነሱም፤ ለእኛም ለአገርም ይበጃል የሚል የጸና እምነት አለዉ። ወያኔ በኢህአዴግ ስም ያሰጠጋቸዉን ምስለኔዎች ጨምሮ ከራሱ ዉጭ ሌላ ማንንም አያምንም፤ ስለዚህም ነዉ የአገሪቱን የመከላከያ፤ የደህንነትና የፖሊስ ተቋሞች በራሱ ሰዎች ቁጥጥር ስር ያደረገዉ። ዛሬ በግልጽ እንደምንመለከተዉ ወያኔ በጉልበት ለያዘዉ ስልጣን ያሰገኛል ብሎ በሚጠረጥረዉ ቦታ ሁሉ የራሱን ልዩ ሚሊሺያ እየለላከ የኢትዮጵያን ህዝብ መኖሪያ ቤቱ ድረስ እየሄደ እያጠቃ ነዉ። ግንቦት ሰባት ወያኔና የፈጠረዉ ዘረኛ ስርዐቱ የቆሙት በፍጹም ማንሰራራት የማይችሉበትት የመጨረሻ መቀበሪያ ጉድጓዳቸዉ ጫፍ ላይ ነዉ የሚል ጽኑ እምነት አለዉ። ሆኖም ጉድጓድ ጫፍ ላይ የቆመ ጠላት በራሱ ተወርዉሮ ጉድጓዱ ዉስጥ አይገባምና ይህንን የተዳከመ ጠላት እተፈራገጠ ጉዳት ከማብዛቱ በፊት ለመደምሰስ ክንዳችንን አጠናክረን በህብረት እንደ አንድ ሰዉ እንነሳ ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

### ቁጫ ወረዳ ዉስጥ አንድ ወጣት እራሱን፤

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ይህ በእንዲህ እንዳለ የቁጫን ጥያቄ ያራምዳሉ የሚባሉ ሰዎች አሁንም ድረስ እየታደኑ መሆኑ የታውቀ ሲሆን ከዚህ ቀደም የወረዳው ህዝብ ያቀረበውን የማንነትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄ አስተጋብታችኋል በሚል የታሰሩት ከ1 ሺ 700 በላይ ሰዎች ቢሆንም በአርባ ምንጭ እስር ቤት ታስረው የሚገኙት ከ246 እንደማይበልጡና ሌሎች በአገዛዙ ሳይገደሉ እንዳልቀሩ በስፋት እየተነገረ መሆኑንም ከዘጋቢያችን ለማወቅ ችለናል።

በተያያዘ ዜናም በወላይታ ሶዶ 18 ሰዎች በውል ባልታወቀ ምክንያት ካለፍርድ ቤት ትእዛዝ ጨለማ ቤት ታስረው እንደሚገኙ ታውቋል። በወላይታ ሶዶ በከፍተኛ ደረጃ የሰብኣዊ መብት ጥሰቶች እየተባባሱ መሆኑን ነዋሪዎች ያጋለጡ ሲሆን ነዋሪዎቹ እንዳሉት ካለምንም ምክንያት የሚያፍኑ የሚያስሩ የሚገርፉ እና ከፍትህ እና ፍርድ ቤት በላይ የሆኑ ትናንሽ ቡድናዊ አገዛዞች እንዳሻቸው በህዝቡ ላይ የሚፈነጩ ካድሬዎች የወላይታን ህዝብ በስቃይ እና በሰቆቃ ውስጥ እያኖሩት መሆኑን ገልፀዋል።

### አዲስ አበባ ዉስጥ አንድ የወያኔ ታጣቂ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የሁለቱን ውዝግብ ቀደም ብለው ያውቁ ስለነበር፣ በራቸውን ዘግተው ከመጠበቅና ከመሸሽ ያለፈ ምንም ዓይነት መከላከልም ሆነ ጩኸት ማሰማት አለመቻላቸውን ተናግረዋል። ተጠርጣሪዉ ዉትድርና ስራዉን ከተወ ረጂም ዘመናት ያለፉ ሲሆን ለምን የጦር ሜዳ መሳሪያ ተሸክም ህብረተሰቡ ዉስጥ ገብቶ እንኖር እንቻለ የዝግጅት ክፍላችን ባለስልጣኖችን ለመጠየቅ ያደረገዉ ሙከራ አልተሳካም። በተለይ ይህ ግለሰብ ሊገድለን ይችላል የሚል ፍርሀት በአካባቢዉ እንዳለ መንግስት እያወቀ ግለሰቡ ክላሺችኮቭ ጠመንጃ ይዞ በሚፈራበትና በሚጠረጠርበት እንዲኖር መፈቀዱ የወያኔ አገዛዝ ለዜጎች መብት ምንም ደንታ እንደሌለዉ ያሳያል የሚሉ ብዙ የህዝብ አስተያየቶች አሉ።

ሁኔታውን ተከትሎ በአካባቢው በርካታ የአዲስ አበባ ቅጥረኛ የፖሊስ ሃይሎች የተበተኑ ሲሆን፡ የሟች ዘመዶችና የአከባቢው ሰዎች በነቂስ በመውጣት የቀብሩን ስራት ለማስፈጸምና የፋሽስቱን ታጣቂ የወሰደው እርምጃ ለምውገዝ ብሎም በየጊዜ የሚፈጸመውን የፋሽስቱ ወያኔ ታጣቂዎችን ግፍ ለማጋለጥ በህብረት ድምጻቸውን ለማሰማት ቢሞክሩም በነዚሁ ቅጥረኛ የፖሊስ ሃይሎች ተበትነዋል። የፋሽስቱ ወያኔ የፌደራል ፖሊስ አመራሮች የአከባቢውን ህዝብ ድብቅ የፖለቲካ አጀንዳ አንግቦ ነው የሚንቀሳቀስ በሚል መሰረት የለሽ ክስ በጅምላ መፈረጃቸው ነዋሪዎችን እጅግ እንዳስቆጣቸው የታወቀ ሲሆን የሟቾቹ ዘመዶችም የኢትዮጵያ ህዝብ ይህን ጉዳችንን ሳይሰማና ሳያውቅልን አንቀብርም ብለው አስከረኖቹን ወደ መኖሪያ ቤት መመለሳቸው ታውቋል።

---

## ከአርማጭሆ የተሰማ ድምፅ

አርማጭሆ ጩኸት በርክቷል። ድብደባው እና እስራቱ ልክ አጥቷል። ምክንያቱ የህወሃት ፍርሃት ነው።ህወሃት ፈርቷል። ፍርሃቱ ሽብር ውስጥ ከቶታል። ባለፈው ሰሞን አማራ ካልሆንኩ ሞቼ እገኛለሁ የሚለው በረከት ስምዖን አርሶ አደሩ ከእኛ ጋር ስለሆነ የሚያስፈራን ነገር የለም ብሎ ነበር። እንዲያውም አርሶ አደሩ *"ታኛ ብንለው ይተኛል፤ተነስ ብንለውም ይነሳል"* ሲልም አክሏል። ይሄ ግን ውሸት ነው። ራሱን እስከዚህ ድረስ አሳልፎ የሰጠ ህዝብ በምን ምክንያት ሌሎችን ትደግፋላችሁ እየተባለ ይታሰራል ተብሎ ቢጠየቅ በረከት ሥምዖን መልስ የለውም።

የአርማጭሆ ህዝብ እምቢ እያለ ነው። እኔ *"ተኛ ስባል የምተኛ፤ተነስ ስባል ደግሞ የምነሳ"* ምናምንቴ አይደለሁም። እኔ በአባቶቼ ጀግንነት ኮርቼ የምኖር ኩሩ ሰው ነኝ። እኔ የአባቶቼን መጠሪያ ምድር አሳልፌ የምሰጥ ደካማ ሰው አይደለሁምም እያለ ነው። ህወሃቶች ይሄን መሰሉን ድምፅ ሰምተው ተሸብረዋል። ይሄ ሽብራቸውም አርማጭሆ እንዲሰፍሩ አድርጓቸዋል።

ታሪክ እንደሚመሰክረው ከሆነ የአርማጭሆ ህዝብ የማንንም ስድብ ተሸክሞ መኖርን የለመደ ህዝብ አይደለም። እንዲሁ ማንም አልባሌ መጥቶ *"ተኛ ሲለው እየተኛ ፤ተነስ ሲለውም እየተነሳ"* ራሱን አዋርዶ መኖርን የሚፈቅድ ዜጋ አይደለም። የአርማጭሆ ጀግንነት ከራሱ አልፎ ሌላውም የሚተርፍ ነው። ህወሃት ግን የአርማጭሆን ጀግንነት አዋርጄ፤ ህዝቡንም ከሰው በታች አድርጌ እገዛለሁ በሚል ቅዥት ውስጥ እየዳከረ ነው። ይሄ ቅዥቱም የእውር ድንበሩን እድሜና ፆታ ሳይለይ ያገኘውን ሁሉ እዲያሰቃይ እያደረገው ነው። አርማጭሆ ላይ ሴቶች፤ ግራ ቀኛቸውን መለየት ያልቻሉ ህፃናት፤ አዛውንት ሽማግሌዎች እየተያዙ ይበረበራሉ፤ ይገረፋሉ፤ ይታሠራሉ። ግንቦት ሰባትን ትደግፋላችሁ፤ አርበኞች ግንባር ልትገቡ አስቧችኋል፤ የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄን ታግዛላችሁ እየተባሉ ቁም ስቅላቸውን ያያሉ። የአርማጭሆ እጣ ፈንታ ይሄው ሁኗል። ጠቅላይ ሚንስትር የሚመስለው ደሳለኝ ኃ/ማሪያም "ግንቦት ሰባት በህልም ዓለም ያለ ነው፤ ከህልሙ እስከሚነቃ እንጠብቀዋለን" ብሎ ነበር። ይሄም ሌላው ውሸታቸው ነው። በህልም ውስጥ ባለ ድርጅት ሥም ለምን ዜጎች እንደሚንገላቱ እና ለምን እንደሚታሠሩ ይሄ ግለሰብ መልስ የለውም። ከዚህ ቀጥለን ግንቦት ሰባት በአገራችን ለውጥ እንዲመጣ ከልቡ የሚሠራ ድርጅት መሆኑን ልናስታውሰው እንወዳለን።

ምንም እንኳን ክልሎች ራሳቸውን በራሳቸው ያስተዳድራሉ ተብሎ ህግ ቢፃፍም ህወሃቶች ግን ከአርማጭሆ ጓዳ ሊወጡ አልፈቀዱም። በየክልሎቹ የፀጥታ ጉዳይ አማካሪ ወይም ደግሞ ልዩ ጥበቃ ተብለው ክልሎችን በመበዝበዝ ተግባር ላይ ተጠምደዋል። በአርማጭሆም ልዩ ጥበቃ ኃይል ነን ሲሉ በህዝቡ ላይ ዘምተዋል። ወደዚህ ዘመቻ የመራቸው ደግሞ ህወሃቶች አርማጭሆን መፍራታቸው ነው።አርማጭሆም ህወሃትን ጠልቷል ንቋልም። በዚህ በተናቀና በተጠላ ቡድን አልገዛም ያሉ ብዙ ዜጎች የምር "ህወሃት በቃ" ማለት መጀመራቸው እና ዘረኛው ህወሃት እችለዋለሁ ብሎ በሚደነፋበት ቋንቋ ለማናገር የአያቶቻቸውን ጋሻና ጦር አንስተው እየተደራጁ ነው። በዚህ ምክንያት ዘረኞቹና "እኔ ብቻ" ማለትን የሚያውቁ ህወሃቶች ተሸብረው ህዝቡንም እያሸበሩት ነው። እውር ድንብራቸውንም ያገኙትን ሁሉ እያሰሩ እና እየደበደቡ የአካል ጉዳት እያደረሱ ይገኛሉ። የአሸባሪነታቸው መገለጫም ይሄው ነው።

መቸስ ስለህወሃት አሸባሪነት ብናወራ ትርፍ የለውም። ህወሃት አሸባሪ ነው። ከፍተኛውን እርዳት የምትለግሰው አሜሪካን ሳትቀር ህወሃትን ከአሸባሪ መዝገብ ልትፍቀው አልፈቀደችም። ምክንያቱም ህወሃት አሸባሪ ድርጅት ነው የሚል ቋሚ እምነት አላት። ይሄ አሸባሪ ቡድን በከፍተኛ ቅዥት ውስጥ ይገኛል። የቅዥቱ ምክንያት ራሱ የፈጠርው ጭካኔ፤ የዘረጋው የዝርፊያ መረብ፤ በግፍ ያፈሠሠው የንፁሃን ደም፤ የኢትዮጵያን ጥቅም በዚህም በዚያም አሳልፎ መስጠቱ እና መሰል እኩይ ተግባሮቹ ናቸው። በዚያች አገር እውነተኛ ፍትህ፤ ዴሞክራሲ፤ እኩልነት እና የህግ የበላይነት ከሠፈነ ህወሃቶች ሊከድኑት የሚሞክሩት እኩይ ተግባሮቻቸው በሙሉ ይገለጣሉ። ይሄ ደግሞ ለህልውናቸው አደጋ ነው። ስለዚህ በዜጎች የሚነሱ የፍትህ፤ የነፃነት እና የእኩልነት ጥያቄዎች ለህልውናቸው አደጋዎች ስለሆኑ በማንኛውም መንገድ ማፈን ብቸኛ አማራጫቸው ሁኗል። ይሄ ብቸኛ መንገዳቸውም ያገኙትን ሁሉ የግንቦት ሰባት ንቅናቄን ጨምሮ አሸባሪ የሚል ቅፅል እንዲለጥፉ አድርጓቸዋል። በአሁን ሠዓት በአርማጭሆ ህዝቡ እየተሰቃየ ያለው የፍትህ፤ የእኩልነት፤ የዴሞክራሲና የነፃነት ጥያቄ ያነሱ ኃይሎችን ትደግፋላችሁ እየተባለ ነው።በዚያ አካባቢ ማሳውን በመንብኘት ላይ የሚገኝ አርሶ አደር ገና ለገና ከግንቦት ሰባት ወይም ከአርበኛ ግንባር ወይም ደግሞ ከትህዴን ጋር ይቀላቀላል በሚል ፍርሃት ተይዞ በማያውቀው ምክንያት በማይታወቁ ቡድኖች እጅ አሣር መከራውን እንዲያይ እየተደረገ ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ቁም ነገር ደግሞ የአርማጭሆ ሰዎች ላይ ግፍ እየፈፀሙ ያሉት ከትግሪኛ ውጪ ሌላ ቋንቋ መናገር የማያውቁ ራሳቸውን "ትግሬ ነን" ብለው የሚጠሩ ቡድኖች መሆናቸው ነው።ከዘረኝነቱ ከበብ ወጥቶ ኢትዮጵያን ማየት የተሳነው ህወሃት ኢትዮጵያን ከተቆጣጠር ግዜ ጀምሮ አገራችን የገባችበት አጣቢቂኝ ህወሃት ከትግሬ ራስ አልወርድ ማለቱ ነው። በትግሬ ሥም ይገድላል፤ በትግሬ ሥም በግፍ ያሥራል፤ በትግሬ ሥም የወንዶችን ብልት ይቀጠቅጣል፤ በትግሬ ሥም ሌሎችን ያዋርዳል።በአጠቃላይ ህወሃት እየፈፀመ ያለው ድርጊት ትግሬ ባልሆነው የህዝብ ክፍል ስነ ልቦና ውስጥ የሚፈጥረው አሉታዊ ተፅእኖ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም። የአርማጭሆ ሰዎች ትግሪኛ ቋንቋ በሚናገሩ ቡድኖች ተይዘው የመታሰራቸውና የመደብደባቸው ነገር ለትውልድ የሚተላለፍ እንዲሚሆን ህወሃቶች አይገነዘቡትም ብለን አናስብም። ህወሃቶች "እኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይበቀል" እንዳለቸው ከብት መሆንን ስለመረጡ ትውልዱን አሻግረው ለማየት ተስኗቸዋል። እናም "ማን አባቱ ምን ያደርገናል" በሚል ትዕቢት ታውረዋል። ይህ የታወረው ዓይናቸው እንዲሁ በከንቱ ያለ ዋጋ እንደማይከፈት በቅጡ መረዳት ከዜጎች ይጠበቃል።

ምንም እንኳ እያንዳንዱ ክልል በአካባቢው ልጅ ፤በሚያውቀው ቋንቋ ተነጋግሮ ክልሉን ያስተዳድራል ቢባልም ህወሃት ከየክልሎቹ ጓዳ ጎድጓዳ ከወጣ የሚሞት ይመስለዋል። በየክልሎቹ ራስ ላይ ቁጢጢ ብሎ ራሱ ከሳሽ፤ ራሱ ፈራጅ ሁኗል። ፍርዱ በቅንነትና በእውነት ሆኖ ቢገኝ በቀልኩበት የሚለውን ጎሳ ያስመሰግን ነበር።የህወሃት ፍርዱ ቅን አይደለም።ክሱም እውነት አይደለም። ህወሃት በህግ ሽፋን ግፍ ይፈፅማል።በንግድ ሥም አገሪቷን ይዘርፋል፤ የግለሰቦችን ኃብት ይቀማል። በያዘው ሥልጣን ህዝብን ያስከፋል ያስለቅሳል።የህወሃት እኩይ ተግባር ነፃ አወጣዋለው ላለው ህዝብ ያተረፈለት በልብ የተቋጠረ ቂም እንጂ ሌላ አይደለም። ከህወሃት ውስጥ ይሄን ግፍ ለማስቆም፤ የህን ቂም በፍቅር ለመቀየር የሚያስብ ሰው የሚሆን ሰው አይገኝም። ይህን መሰሉን ችግር ለመፍታት ምኞቱ ያላቸው የትግራይ ምርጥ ልጆች በህወሃት ተበልተው አልቀዋል። የቀሩትም በሃዘን ተውጠው ዝምታን መርጠዋል። ከእንግዲህ ከህወሃት የሚጠበቅ ምንም በጎ ነገር የለም። የቀረን አንድ አማራጭ ህወሃትን ማስወገድ ብቻ ነው።

የአርማጭሆ ህዝብ እንደ ጋምቤላው፤ እንድ አጋዴኑ፤ እንደ አፋሩ ሁሉ ሮሮ ውስጥ ይገኛል። ይሄ ሮሮ ግን ማብቃት አለበት። ሮሮ ነፃነትን አያመጣም፤ ልቅሶም ክብርን አይመልስም።የአርማጭሆ ህዝብ ከአያት ከቅደም አያቶቹ የወረሰው ኩራትና ጀግንነት ያለው ህዝብ ነው። ማንም አልባሌ መጥቶ *"ተኛ ሲለው የሚተኛ፤ተነስ ሲለው የሚነሳ "* ፈሪ ህዝብ አይደለም። አሁን እንምቢ ለክብሬ፤ እንምቢ ለርስቴ ማለቱን አጠናክሮ መቀጠል አለበት።

እኛም በግንቦት ሰባት ዙሪያ የተሰብሰብን ዜጎች ይሄን የመከራ ምንጭ የሆነውን ህወሃትን አደብ ለማስገዛት የምንችለውን ሁሉ እያደረገን ነው፡፡ ሁለገብ ትግላችን መሥመር ይዟል። በርካቶች አብረውን የፍትህ፤የነፃነትንና የእኩልነትን ጥያቄ አንግበው ተነስተዋል። እኛም የአያቶቻችንን ጋሻና ጦር አንስተን ለፍትህ፤ለእኩልነት እና ለነፃነታችን የምናደርገውን ትግል አጠናክረን እየቀጠልን ነው። ከእንግዲህ የሚመልሰን የለምና የአርማጭሆ ህዝብ ዝም አትበል። ህወሃት በእጣ ፈንታህ ላይ ወሳኝ ሆኖ እንዲቀጥል አትፍቀድለት። ህወሃትን በሚገባው ቋንቋ ለማናገር ከተነሱ ወገኖችህ ጎን ቁም እና የአባቶችህን ጀግንነት ታሳይ ዘንድ ጥሪያችንን እናቀርብልሃለን። እኛ ሳናቅማማ ተነስተናል። የአርማጭሆ ህዝብም ለክብርህ፤ለነፃነትህ እና ከአባቶችህ ለወረስከው የደም መሬት ስትል ሳታቅማማ ተንስ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

## 118ኛው የአድዋ ድል በዓል ባለፈው እሁድ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

አንዳንድ ከአዲስ አበባና ከተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ያገኘናቸው አስተያየቶች እንደሚያስረዱት ደግሞ "በሀገራችን የአድዋ ድል ቀንን ለማክበር የግድ ወያኔ ሕወሃት ፈቃድ መስጠት እንዳለበት የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ገጠመኝ በማስታወስ ካስረዱ በኋላ፤ "በዚህ ዘመን በኢትዮጵያ እየኖሩ በአድዋ ድል በአል ጮቤ መርገጥ ማለት በእስር ቤት ተቀምጠው እስር የተፈረደበት አዲስ ታሳሪ ሊያስሩት የመጡትን ጉልበታሞች አሸንፎ ብትንትን ሲያደርጋቸው የሚአሳይን ፊልም ተመልክቶ እንደመደሰት ያለ ነው። ምክንያቱም ያ ትእይንት ከእስር አያስፈታወትምና" ካሉ በኋላ "አባቶቻችን ጀግኖች ነበሩ። ይህ ምንግዜም የማይካድ በደማቁ የተጻፈ ታሪክ ነው። ነገር ግን እኛም የራሳችን የሆነ ያባቶቻችን ሳይሆን የኛ የምንለው ታሪክ መስራት ይጠበቅብናል። ፋሽስት ወያኔን ማስወገድ አፍንጫችን ስር ያለና የእኛን ታሪክ ሰሪነት እየጠበቀ ያለ ጥሩ አጋጣሚ ነውና በቁርጠኝነት እንነሳ" በማለት አጠቃለዋል።

የአደዋ የድል በአል ቀን፤ ፋሽስት ጣሊያኖች፣ በጥቅሉ የአድዋ ጦርነት ተብሎ በሚጠራው ውጊያ በመጀመሪያ በአምባላጌ ቀጥሎም በመቀሌ በመጨረሻም በአድዋ በተደረጉ የተለያዩ የጦር ግንባሮች ታዋቂ የጦር ጄኔራሎቻቸውን ሳይቀር እያስማረኩ በፍጹም የኢጥዮጵያዊያን የበላይነት ሽንፈትን የቀመሱበትና ኢትዮጵያዊያን አባቶቻችንም አይበገሬነታቸውን ያስመሰከሩበት በመሆኑ በየዓመቱ በደማቁ የሚከበር የድል በአል መሆኑ ያታወሳል።

..............................................................................................................

## የአቶ አለማየሁ አቶምሳ ዜና እረፍት ኦሮምያ ዉስጥ የተለያዩ ስሜቶችን ፈጥሯል

የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንንት ሆነዉ ከተሾሙበት ግዜ ጀምሮ ለህክምና ታይላንድ ሲመላለሱ የነበሩት የ45 አመቱ ጎልማሳ አቶ አለማየሁ አቶምሳ አዚያዉ ታይላንድ የህክምና እርዳታ እየተደረጋላቸዉ ሳለ ማረፋቸዉ የተሰማዉ በዚሁ ባሳለፈነዉ ሳምንት ዉስጥ ነበር። አቶ አለማየሁ በቅርቡ በጤና ችግር የተነሳ እራሳቸዉን ከሀላፊነት ማግለላቸዉ ይታወሳል። የአቶ አለማየሁን እረፍት ተከትሎ የኦህዴድ አባላትና የክልሉ ነዋሪዎች ስለአሟሟታቸው ሚስጢር የተለያዩ መላምቶችን እያቀረቡ በመነጋገር ላይ መሆናቸውን ያሰባሰብነው መረጃ ያመለክታል። አብዛኛው ህዝብ ግለሰቡ በተቃዋሚዎቻቸው ተመርዘው መሞታቸውን በማመን የአሟሟታቸው መንስኤ እንዲታወቅ ይፈልጋል።የኦህዴድ አባላትም በጉዳዩ ላይ እየተወያዩ ሲሆን ችግሩ በአመራሩና በአባላቱ መካከል መከፋፈል እንዳይፈጥር አንዳንድ የድርጅቱ አባላት መግለጫ እንዲሰጥ ግፊት እያደረጉ ነው። የፕሬዚዳንቱ የግል ጠባቂ የሆነው ግለሰብ በተመሳሳይ በሽታ ላይ መገኘቱ ለጥርጣሬው በር እንደከፈተ ለማወቅ ተችሎአል። አቶ አለማየሁ የኦህዴድ ሊቀመንበርነታቸውን በገዛ ፈቃዳቸው ሳይለቁ እንደለቀቁ ተደርጎ የተለቀቀው ዜናም መነጋገሪያ መሆኑን ከድርጅቱ አባላት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

አቶ አለማየሁ መሞታቸው እንደተሰማ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአዲስ አበባ ለሚገኙ ሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች ፣ በከተማው የሚገኙ የኦህዴድ አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ሌሎች የኢህአዴግ ደጋፊ አባላት እንዲገኙና አስከሬን እንዲቀበሉ በማሰብ በከተማው ለሚገኙ ሁሉም የመንግስት መ/ቤቶች አስቸኳይ የስልክ መልዕክት ተላልፏል።የአስክሬን አቀባበሉን ውጤታማና የተሳካ ለማድረግ ከመንግስት የስራ ሰዓት ውጭ ተሸከርካሪና ነዳጅን ጨምሮ ቀላል የማይባል የመንግስት ሃብት ይፈሳል በማለት የመስተዳደሩን ውሳኔ በመቃወም የመስተዳድሩ ሰራተኞች አስተያየታቸውን ገልጸዋል።

ከአባታቸው አቶ አቶምሳ ሚጃ እና ከእናታቸው ወይዘሮ አየለች ብሩ በ1961 ዓ.ም ነው የተወለዱት አቶ አለማየሁ፣ የ3 ልጆች አባት ነበሩ።የኦሮሚያ ምክር ቤት የአዲሱን ፕሬዚዳንት ሹመት ለማጽደቅ በሚቀጥለው ሳምንት ሊያደርገው የነበረውን ስብሰባ ላልተወሰነ ጊዜ ማራዘሙ ታውቋል። አቶ አለማየሁን እንዲተኩ አቶ ሙክታር ፣ አቶ አብዱላዚዝና ወ/ሮ አስቴር ማሞ በእጩነት መቅረባቸውን ለማወቅ ቢቻልም፣ ካፒታል የተሰኘው በአገር ቤት የሚታተም የእንግሊዝኛ ጋዜጣ፣ በሰበር ዜናው ወ/ሮ አስቴር ማሞ ፕሬዚዳንት ሆነው መመረጣቸውን ይፋ አድርጓል። ኢሳት የመረጃውን ትክክለኛነት ለማጣራት ሙከራ ቢያደርግም አልተሳካለትም።

## 12 ሺ ቶን ቡና በተጭበርበረ ሰነድ ወደ ውጭ አገር መላኩ ታወቀ

ለብዙ አመታት የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ዋልታ በመባል የሚታወቀዉ ቡና በወያኔ ዘመን ለሙስና የተጋለጠና የትልልቆቹን የወያኔ ባለስላጣኖችና የቤተሰቦቻቸዉን ኪስ የሚሞላ የንግድ ዘርፍ መሆኑን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙና ለወያኔ ቅርበት ያላቸዉ የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢዎች ከሰሞኑ በላኩልን ዜና ገለጹ። ከአዲስ አበባ በሚደርሱን ዜናዎቸ መሰረት በየአመቱ ብዛት ያለዉ የቡና ምርት በተጭበረበረ መንገድ ለአለም ገበያ የሚቀርብ ሲሆን ከያነኑ ያክል የቡና ምርት ደግሞ ማን እንደወሰደዉና ዬት አንደገባ ሳያታወቅ ጠፋ ተብሎ እንደሚነገር ለማወቅ ተችሏል። ለምሳሌ መለስ ዜናዊ ስልጣን ላይ በነበረበት ወቅት የራሱ ባለቤትና ደጋፊዎቿ የሰረቁትን አንድ መቶ ሺ ቶን ቡና የገባበት ቦታ አልታወቀም ብሎ ከቡና ነጋዴዎች ጋር አስጥ አገባ ዉስጥ መግባቱ የሚታወስ ነዉ።

የስነምግባር እና ጸረ ሙስና ኮሚሽን በቅርቡ በቡና አስተዳደር ላይ የሚታየውን ችግር አስመልክቶ ያወጣውን ሪፖርት ተከትሎ 12 ሺ ቶን ወይም 1 መቶ 20 ሺ ኩንታል ቡና በተጭበረበረ ሰነድ ወደ ውጭ ተልኮ መሸጡን አመልክቷል። ኮሚሽኑ ቡናው በማን በኩል ተሰርቆ እንደተላከ እያጣራ መሆኑን የዘገበው ሪፖርተር፣ የሽያጩ ገንዘብም ወደ አገር ውስጥ አለመግባቱን ገልጿል።ዛሬ ባለው የአለም የቡና የመሸጫ ዋጋ 120 ሺ ኩንታል ቡና ከ16 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወይም ከ300 ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያወጣል። ይህን ያክል ገንዘብ በአንድ ጊዜ በተጭበረበረ ሰነድ መዝረፍ የሚቻልባት አገር ሆናለች የሚለው ዘጋቢያችን፣ ድርጊቱ መንግስት አለ ወይ ያሰብላል ሲል ሃሳቡን አሰፍሯል።

አቶ መለስ በስልጣን ላይ በነበሩበት ወቅት 10 ሺ ኩንታል ቡና መጥፋቱ ይታወቃል። ስለዚሁ ጉዳይ ጥያቄ የቀረበላቸው አቶ መለስ መንግስታቸው እያጣራ መሆኑን ተናግረው ነበር። ይሁን እንጅ የምርመራው ውጤት ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ የታወቀ ነገር የለም።ዘጋቢያችን እንደሚለው ጸረ ሙስና ኮሚሽን እየመረመርኩ ነው ቢልም፣ የምርመራው ውጤት ታፍኖ ሊቀር የሚችልበት እድሉ ሰፊ ነው። በጉዳዩ ዙሪያ የንግድ ሚኒስቴር ባለስልጣናትን ለማግኘት የተደረገው ሙከራ አልተሳካም።

## ወያኔ የራሱን ጋዜጠኞች ሰብስቦ በጋዜጠኞች ጉዳይ ላይ ሊመክር ነዉ

ባለፈዉ ታህሳስ ወር መጨረሻ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅትና የኢትዮጵያ ፕሬስ በጋራ ሆነዉ አጠኑት በተባለዉና በይዘትና በሂደት ላይ ሳይሆን በሰባት የግል መጽሔቶች ላይ በተኮረዉ ጥናት ይዘት ላይ የሚወያይ ከፍተኛ የመንግስት ባለልጣናትና አገዛዙን የሚደግፉ ጋዜጠኞች ብቻ የሚገኙበት ስብሰባ በያዝነው ሳምንት መጨረሻ በአዳማ እንደሚካሄድ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ጠቆሙ።

የመንግስት ድጋፍ ያላቸው የጋዜጠኛ ማህበራት ከመንግስት የኮምኑኬሽን ጽ/ቤት ጋር በመተባበር እንዳዘጋጁት በተነገረለት ስብሰባ ላይ ከ100 በላይ የመንግስትና በገዥው ፓርቲ ደጋፊነት የሚፈረጁ የግል ጋዜጦች ይሳተፋሉ ተብሎ ይጠበቃል። በዚሁ ስብሰባ ላይ አወዛጋቢ የሆነውና በታህሳስ ወር 2006 መጨረሻ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የፊት ገጽ ላይ ይፋ የተደረገው የሰባት መጽሔቶች የአዝማሚያ ጥናት ቀርቦ ውይይት ይደረግበታል ተብሎአል።

የአዲስዘመን ጋዜጣ አሳታሚ የሆነው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትና እና በህግ በፈረሰ ስም እስካሁን የሚጠቀመውና በመንግስት ኮምኒኬሽን ጽ/ቤት ስር አንድ መምሪያ ሆኖ የተዋቀረው የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት አጥንተነዋል ባሉት የአዝማሚያ ጥናት መሰረት አዲስ ጉዳይ ፣ፋክት፣ ሎሚ፣ ቆንጆ፣ ጃኖ፣ዕንቁ እና ሊያ የተባሉ መጽሄቶች ከመስከረም 1/2006 እስከ ህዳር 30/2006 ዕትሞቻቸው የፖለቲካ ስርአቱን የሚያጨልሙ፣ የአመጽ ጥሪዎችን የሚያቀርቡ፣ የኢኮኖሚ እድገቱን የሚያጥላሉ፣ ህገመንግስቱን የሚያዋድቁ፣ የመንግስት ባለስልጣናትን የሚያጥላሉ፣ ሽብርተኝነትን የሚያበረታእና የመሳሰሉት ዘገባዎችን ማቅረባቸውን አጥኚዎቹ ማረጋገጣቸውን መግለጻቸው ይታወሳል።

ይህ ጥናት መንግስት በቀጥታ በፕሬሶቹ ላይ ለመውሰድ ያሰበው እርምጃን ሕጋዊነት ለማላበስ የተዘጋጀ መሆኑን በመጥቀስ ከፍተኛ ትችቶች ሲቀርቡበት ቆይቷል።በዚህ ሳምንት ዓርብ እና ቅዳሜ በአዳማ ይካሄዳል የተባለው ስብሰባ ምናልባት ወደቀጣይ ሳምንት ሊራዘም እንደሚችል የጠቀሱት የመንግስት ምንጮች፣ እስካሁን ባለው መረጃ ስብሰባው በዚህ ሳምንት ይካሄዳል የሚል ነው።በስብሰባው ላይ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጽ/ቤት ሃለፊ አቶ ሬድዋን ሁሴን በፕሬሶቹ ላይ የተካሄደው ጥናት ትክክለኝነት ለጋዜጠኛው ያስረዳሉ ተብሎ ይጠበቃል።

## ከበረራ ቁጥር 702 አውሮፕላን ጠለፋ ወዲህ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ሙስና መነገር ከሚገባው በላይ ንሯል፣ አብራሪዎችም ሆኑ ሌሎች ሰራተኞች እውቀታቸው፣ ችሎታቸውና ልምዳቸው ተዘንግቶ በሕወሃት ቁንጮዎች ይሁንታ ብቻ ስራ ያገኛሉ ወይም ይባረራሉ፤ ብዙ ልምድ ያላቸው አብራሪዎች በየምክንያቱ እየተዘለሉ ወይም እየተባረሩ የውጭ አብራሪዎች በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ይቀጠራሉ። በጥቅሉ ድርጅቱ በስብሷል። አንድን ወይም የተወሰኑ ሰዎችን በማባረር ወይም በመለዋወጥ ማስተካከል አይቻልም። ችግሮች ሲፈጠሩም የአእምሮ ችግር ያለባቸው ሰዎች ከወኑት በማለትም ችግሮችን ማስወገድ አይቻልም። አየር መንገዱ ያለ ሕወሃት ተጽእኖ ራሱን ችሎ ሊነቀሳቀስ ይገባዋል። የችግሮቹ ሁሉ ምንጭ ሕወሃት ነውና” ብለዋል።

ከዚህ በፊት የወረዳ ዋና ከተማነት ይገባናል በሚል በዋካ ከተማ ተነስቶ በነበረው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግና ሕዝብን በማስተባበር የሚታወቀው መምህር የኔሰው ገብሬ በሀገሪቱ የነገሰውን አፈና፣ ዘረኝነትና የመልካም አስተዳደር እጦት ከማይ ሞቴን እመርጣለሁ ብሎ በሕዝብ ፊት ራሱን አቃጥሎ ለወገኖቹ መስዋእት በሆነበት ወቅት የወያኔ ሚዲያዎችና የማህበራዊ ድረገጾች ወኪሎቹ የየኔሰው ገብሬ እህት ያሏትን ፊታውራሪ አድርገው በማስከደም የኔሰው ገብሬ የነጻነት ታጋይ፣ ለሕዝቡ ለወገኑ ሲል ራሱን መስዋእት ያደረገ ሳይሆን እብድ ስለነበረና ራሱን መቆጣጠር ስለማይችል ነው ራሱን ያቃጠለው ማለታቸው አይዘነጋም።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## እነዚህ ሰዎች የሚናገሩትንም አያውቁም !

(ሲሳይ አባተ - ከአዲስ አበባ) - ክፍል 1

የሕወሓት መንግሥት በአገዛዝ ዘመኑ ከተሳኩለት ነገሮች አንዱና ዋነኛው የቀብር ሥነ ሥርዓቶችን ባማረ ሁኔታ ማከናወን ነው። ባለፉት ዓመታት ከተከናወኑ የቀብር ሥነ ሥርዓቶች ውስጥ ለምሳሌ የሀየሎም አርአያ፣ የጭራቁ መለስ ዜናዊና የትዳር አፋቹ የወንበዴው ጳጳስ የጳውሎስ ደማቅ የልቅሶና የቀብር ሥነ ሥርዓቶች በዋቢነት የሚጠቀሱ ናቸው። የጥላሁን ገሠሠን ያላካተትኩት የሕዝብና የሀገር ልቅሶና ሀዘን ስለነበረ ነው። እንጂ በሀገር ደረጃ ካየነው የጥላሁንን የመሰለ ደማቅ ልባዊ ሀዘን የተገለጸበት ልቅሶ ታይቶ የሚታወቅ አይመስለኝም። በጥላሁን ቀብር ሕዝብ በዐዋጅና በማባበያ ወጥቶ እንዲለቀስ አልተደረገም። በጥላሁን ቀብር የሀገር ሀብት ከካዝና እየተመዘረጠ ከናቴራና ኮፍያ እየተገዛ ፖስተርም እየተለጠፈ፣ የውሎ አበልም እየተከፈለ በመቶ ሚሊዮኖች የሚገመት ገንዘብና ማቴሪያል እንዲባክን አልተደረገም። በጥላሁን ቀብር ሕዝብ በግዳጅ እንዲያለቅስና ከሥራ እየቀረ ከአንጀቱ ሳይሆን ከአንገቱ እንዲያላዝን አልተደረገም። የሰሜን ኮርያን ልቅሶ የሚያስንቅ የግዳጅ ልቅሶ ያዬነው በመለስ ዜናዊ ቀብር ነው - በሀፍረት የለሹ ወያኔ አስገዳጅነት።

ዛሬ ደግሞ ግራ የተጋባ ልቅሶ እያየን ነው። የሰዎች መሞት በውነቱ ያሳዝናል። አቶ አለማየሁ አቶምሳ ሞቷል - በሰውነቱ ከልብ እናዝናለን። በሆዳምነቱና ከታሪካዊ ጠላቶቹ ጋር ተባብሮ ለሀገር መቀበር በመታገሉም እንዲሁ እናዝንበታለን፤ ለማንኛውም ፈጣሪ ነፍሱን ይማር - አፈሩንም ገለባ ያድርግለት። ለልጆቹና መላ ቤተሰቡ አጽናኝ መላእክትን ይዘዝላቸው። በመሠረቱ ሰውዬው የሞተው ዛሬ አይደለም። የሞተው የዛሬ ሦስት ዓመት ገደማ ናዝሬት ውስጥ ታካሄደ በተባለ የኦህዴድ ጉባኤ ላይ ጓደኞቹ ይሁኑ ሌላ ወገን በሚጠጣው ይሁን በሚበላው ነገር ላይ መርዝ በሰጡት ጊዜ ነው። ወያኔ ራሱ ገድሎ  ሙሾ ማውረድን የተካነበት በመሆኑ ራሱ የገደለውን አለማየሁ በድምቀት እየሸኘው ነው። ዕንቆቅልሹ ወያኔ ከንፈ የሚባለውን የደህንነት ኃላፊውን ባስገደለበት ወቅት እንዴት በመሰለ ሁኔታ ቁንጮው ጭራቅ መለስ እያለቀሰ እንደሸኘው የምናስታውሰው ነው። እስስቶች ናቸው።

የዛሬው ግራ አጋቢ የልቅሶ ሥነ ሥርዓት ምን ይመስላል? ሬሣው በዓለም እንደሚታወቀው ከአንገቱ በላይ እንዲታይ አልተደረገም። በኔ ግምት ይህ ያልሆነበት ምክንያት የፈራረሰው የመለስ አስከሬን ተሸፍኖ እንደተሸኘ ሁሉ ይህንንም ሰውዬ የእርሱ መናጀ በማድረግ የመለስ አስከሬን ሁኔታ እንዳይታወስና መነጋገሪያ እንዳይሆን ነው። አስከሬንን አለማሳየት ባህላቸው ነው እንዲባልና የመለስን መፈራረስ ለማስረሳት የፈለጉ ይመስለኛል። እንጂ የአለማየሁ ሰውነት እንደመለስ የፈራረስ አይመስለኝም። አንደኛ ነገር ይህ ሰው የሞተው ሰሞኑን ስብሰባ እያካሄደ በነበረበት ጊዜ ድንገት ተስለምልሞ በመውደቅና ከዚያም ወዲያውኑ ወደውጪ ተልኮ የህክምና ርዳታ ተደርጎለት ነው። ስለዚህ ጭንቅላቱም ሆነ ፊቱ ገና ‹ፍረሽ› ነው። ሁለተኛ ከሞተም በኋላ እንደመለስ ለወራት አልተደበቀም፤ የተፋጠነ የቀብር ሥነ ሥርዓት ነው እየተደረገለት ያለው። በዚህች በቀብር ሥርዓት እንኳን ከሕወሓት ውጪ ያሉ ሌሎች ወገኖች መወሰን አልቻሉም ማለት ነው።

ይህ ሀዘን ክልላዊ እንጂ ፌዴራላዊ አይደለም። የፕሮቶኮል ጉዳይ ያነጋግራል። ባንዴራ ዝቅ ተደርጎ መውለብለብ ያለበት ሰውዬው ይመራው ነበር በሚባለው "ክልላዊ መንግሥት" እንጂ በመላዋ ኢትዮጵያ መሆን አልነበረበትም። ስህተት ነው። አወሳሰኑ ራሱም ስህተት ነው። አንድ ግለሰብ ወይም የጥቂት ግለሰቦች ውሳኔ ይመስላል። የተሰበሰበ የፓርላማ ጉባኤ ሳይኖር ጥቂት ሽፍቶች እንደፈለጉ የሚያዙበትና የሚናዝዙበት መንግሥት ያለን ለመሆናችን አንደኛው ዋቢ ነው። ለማስመሰልም እንኳን አልቻሉበትም። ለወትሮው የማስመሰል ሁኔታ ይታይ ነበር፤ የዐይን ጥቅሻ ብቻ እያዩ የሚያጨበጭቡበና በረጃጅም ዲስኩሮች ወቅት ደግሞ እያዛጋና እያንጎላጀ እንቅልፉን የሚለጥጥ ፓርላማ ያለን እኛ ብቻ ነን - ዕድሜ ለወያኔ። አሁን አሁን የነበረው ጥቂት የማስመሰል ትያትር በጭራሽ ጠፍቷል።

ከአንድ ጎሬ ውስጥ የተደበቀ ሥውር መንግሥት ሳይኖር አይቀርም። ያ ሥውር ወያኔዊ ኃይል የመንግሥት ወንበሮች ላይ በጎለታቸው እነኃይለማርያምንና ተሾመን የመሳሰሉ ሆዳሞች አማካይነት በስልክ በሚተላለፍ ቀጥተኛ ትዕዛዝ ሀገሪቱን እንደፈለገ መንዳቱን ቀጥሏል።

ሬሣው መልበስ ያለበት የክልሉን ባንዴራ መሆን ሲገባው በአንድ በኩል የወያኔን የኢትዮጵያ ባዴራ አልብሰው በሌላ በኩል ደግሞ ኦሮምያ የሚባለውን አዲስ ወያኔ ሠራሽ ሀገር ባንዴራ አልብሰውታል። አስከሬኑ የሚመስለው አስከሬን ሳይሆን የተለያዩ ቀለማት ባላቸው ጨርቃ ጨርቆች ያሸበረቀ የጠንቋይ ቤት የመጠንቆያ ክፍል ነው። ቋንቋቸው ደግሞ የበለጠ ግራ ያጋባል።

እነዚህ ሰዎች የቃላት አጠቃቀማቸው ራሱ አስገራሚ ነው። ጭራቁ መለስ ሲሞት ደደቧ ሚስቱ "መለስ ተሰዋ" ብላ በሀዘናችን መሃል አሳቀችን። አንድ ሰው ተሰዋ የሚባለው በጦርነት ላይ ሲሞት ወይም ለግዳጅ በሄደበት ሳይመለስ ሲቀርና ሕይወቱ በዚያው ሲያልፍ ነው። እንጂ በሰላም ሀገር ታሞ የሞተን ሰው ተሰዋ ማለት የቋንቋ ችግርን ከማሳየቱ በስተቀር ሌላ ትርጉም የለውም። በውነቱ ማይምነት ነው። በሌላ ወገንም የመንግሥት ሥልጣን ከያዙ ከ23 ዓመታት በኋላ "ታጋይ" እያሉ ሰዎቻቸውን ሲጠሩ ስንሰማ ምን ማለት እንደፈለጉ አይገባንምና መቸገራችን አይቀርም። ታጋይ የሚባለው በትግል ወቅት ነው። አሁን ባለሥልጣን ሊያውም የአሜባን ቅርፅ ይዞ ከኤርትራ በስተቀር (ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል)

## ጣሊያን አባይ ወንዝን አስመልክቶ ኢትዮጵያንና

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የተፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት መሞከር ብቻ ነው ብለዋል።አህራም ለተባለው የግብፅ ጋዜጣ የተናገሩት አምባሳደሩ፣ በኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ላይ እየተሳተፈ የሚገኘው ሳሊኒ በመባል የሚታወቀው የጣሊያን ኩባንያ የግል መሆኑንና የጣሊያን መንግሥትም በግል ኩባንያዎች ላይ ምንም ዓይነት ሥልጣን እንደሌለው አስታውቀዋል።

‹‹የጣሊያን ሕግ የግል ኩባንያዎች የትም አገር ተዘዋውረው መሥራት እንደሚችሉ ዋስትና ይሰጣል፤›› በማለት የመንግሥታቸውን አቋም ግልጽ አድርገዋል። የግብፅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ወደ ጣሊያን በተጓዙበት ወቅት የተነገራቸውም ጣሊያን በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል ያለውን አለመግባባት ለመፍታት እንደምትሠራ ብቻ ነው ብለዋል።

የግብፅ መንግሥት የውኃ ድርሻዬ ይቀንሳል በማለት ከሚያቀርበው ተቃውሞ በተጨማሪ የግድቡ ግንባታ የጥራት ደረጃ ሌላኛው መከራከሪያ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት በግልጽ በተደጋጋሚ የግብፅ የውኃ ድርሻ እንዳይቀንስ በይፋ አሳውቋል። በመሆኑም በግብፅ ላይ ጉልህ የሆነ ጉዳት እንደማያደርስ እየገለጸ ነው። የግድቡ ግንባታን በተመለከተም ሳሊኒ የተባለው ኩባንያ በዘርፉ ከፍተኛ የሆነ ብቃት እንዳለውና ግድቡም ጥራቱን ጠብቆ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተገነባ እንደሆነ አስታውቋል።

የአባይን ወንዝ ዉኋ መጠን በተመለከተ በቅርቡ አንድ ከፍተኛ የግብጽ ባለስልጣን "የግብፅ የዓባይ ውኃ ድርሻ የማይታለፍ ቀይ መስመር ነዉ" ብለዉ መናገራቸዉ የተሰማ ሲሆን ቀዩ መስመር የተሰመረዉመና ሲታለፍ ታለፈ የሚባለዉ አባይ መዳረሻ ግብፅ ዉስጥ ይሁን ወይም የአባይ መነሻ ኢትዮጵያ ዉስጥ ይሁን ባለስልጣኑ የተናገሩት ነገር የለም። የግብፅና የኢትዮጵያ ጉዳይ አለም አቀፍ ትኩረት እያገኘ ሲሆን ብዙ የአለም ድፕሎማቶች ጉዳዩ በምንም መልኩ ከጠረቤዛ ዙሪያ ዉጭ መፍትሄ ሊያገኝ እንማይችል በመናገር ላይ ናቸዉ"።

ግድቡን በመገንባት ላይ ያለው ሳሊኒ ኮንስትራክሽን ኩባንያ በአውሮፓ፣ በእስያና በአፍሪካ ከሃያ በላይ ግድቦችን በመገንባት የሚታወቅ ሲሆን፣ በኢትዮጵያም ግልገል ጊቤ ሁለትና ጣና በለስ የኃይል ማመንጫዎች ገንብቷል። በአሁኑ ጊዜ ግልገል ጊቤ ሦስትንም እየገነባ ነው። ባለፈው ወር ኢትዮጵያን የጐበኙት የጣሊያን ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከእንግሊዘኛው ዘ ሪፖርተር ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፣ በኃይል ማመንጫ ግድብ ግንባታ ሳሊኒ የተባለው የጣሊያን ኩባንያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ልምድ ማካበቱን ተናግረዋል።

ለግድብ ግንባታ የሚያስፈልገውን ብቃት ሳሊኒ በሚገባ እንዳለው የተናገሩት ምክትል ሚኒስትሩ፣ ሳሊኒ በኢትዮጵያ እያከናወነ ያለው ግንባታ የኢትዮጵያ ፕሮጀክት እንጂ በጣሊያን መንግሥት የገንዘብም ሆነ ምንም ዓይነት ድጋፍ እንደማይደረግለት ጠቁመዋል። ይህ በዚህ እንዳለ፣ የግብፅ የመስኖ ሚኒስትር በመሆን በድጋሚ የተመረጡት መሐመድ አብዱል ሙታሊብ ባለፈው ሰኞ በሰጡት መግለጫ፣ ‹‹ግብፅ ከዓባይ ውኃ ስታገኝ የነበረው ድርሻ የማይታለፍ ቀይ መስመር ነው፤›› አሉ። የግብፅ ጊዜያዊ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር ባለፈው ሳምንት በገዛ ፈቃዳቸው ካቢኔያቸውን መፍረሳቸውን ተከትሎ የተሰየመው የአገሪቱ ጊዜያዊ መንግሥት ውስጥ በድጋሚ የመስኖ ሚኒስትር ሆነው የተመረጡት ሙታሊብ፣ ‹‹የኢትዮጵያ መንግሥት እየገነባ ባለው የህዳሴው ግድብ ላይ በጣም ግትር ሆኗል፤›› ሲሉ ወቅሰዋል።

ግብፅ በኢትዮጵያ ውስጥ ልማት እንዲኖር ከማበረታታት አልፋ ትደግፋለች የሚሉት የመስኖ ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያ ግብፅን ሳትጐዳ የዓባይን ውኃ መጠቀም ትችላለች ብለዋል። ነገር ግን ይህንን አስተያየት በሰጡበት አንደበታቸው ተመልሰው ‹‹የግብፅ የውኃ ድርሻ የማይታለፍ ቀይ መስመር ነው፤›› በማለት ተናግረዋል። ባለፈው ሳምንት ዕትም የግብፅ ባለሥልጣናት በህዳሴው ግድብ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ዓለም አቀፋዊ ገጽታ ለማላበስ እያደረጉ ያለውን ጥረት መዘገባችን ይታወሳል።

ከእነዚህም መካከል የህዳሴው ግድብ ግንባታን እያከናወነ የሚገኘው ሳሊኒ የተባለው የጣሊያን ኩባንያ ግንባታውን አቁሞ እንዲወጣ የሚያደርጉት ጥረት በዋናነት ይገኝበታል። ግብፆች በተለያዩ ጊዜያት በሚያንፀባርቁዋቸው ተለዋዋጭ አቋሞችና በማያቋርጡ ዘመቻዎች ላይ አስተያየታቸውን የሚሰጡ ዜጐች፣ መንግሥት እግር በእግር እየተከታተለ ዘመቻውን ማክሸፍ አለበት ይላሉ። ግድቡ ለአንዲት ሰከንድ ግንባታው አይቋረጥም ማለት ብቻ ሳይሆን፣ የግብፅ ባለሥልጣናትንና ሚዲያዎች ዘመቻ ያለመዘናጋት ማክሸፍ የወቅቱ ዓብይ ጥያቄ መሆኑንም ያሰምሩበታል።